# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 144 የካቲት 10 2003 ገጽ 1


**አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!**

**የኢትዮጵያ ወጣት ከቱኒዝያ፣ ግብፅ እና ከሰሜን አፍሪቃ አቻወቹ መማር ያለበት አምስት ቁም ነገሮች፡- ድርጅት፣ የመረጃ ልውውጥ፣ መቻቻል፣ በራስ የመተማመን ስሜት፣ መብት ክብር እና ባለቤትነት ዋናዎቹ ናቸው። ጊዜ የለም። ሁኔታዎች በፍጥነት እየተቀያየሩ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ወጣት ለመብቱ፣ ለክብሩና ለሃገሩ ሲል ዛሬውኑ ይነሳ!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ለመውደቅ አደጋ ላይ ካሉት ሃገራት ውስጥ ዋነኛው ነው ተባለ

በአሜሪካን ሃገር የሚገኙት ዋይኔ ማድሰን በመባል የሚታወቁት ታዋቂ ጥናታዊ ጋዜጠኛ አር ኤስ ከተባለ የቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ባደረጉት ውይይት አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለመውደቅ አደጋ ላይ ካሉትና ተራቸውን ከሚጠብቁት አገዛዞች መካከል ዋነኛው ነው በማለት ተናግረዋል::

ዋይኔ ማድሰን በሰሜን አፍሪቃ የተነሳውን ህዝባዊ አመጽ አስመልክቶ ሲናገሩ አሁን ጥያቄው አምባ ገነናዊ አገዛዝ ባለባቸው ሃገራት ውስጥ አመጽ ይነሳል ወይንም አይነሳም የሚለው ሳይሆን፣ ስልጣኑን ጥሎ እንዲፈረጥጥ የሚደረገው ተረኛው የሃገር ቁንጮ የትኛው ነው የሚለው እንደሆነ ገልጸዋል:: አያይዘውም ነጻነትን የተጠማ ህዝብ እንኩአን በየሃገራቱ የህዝብን ቁጣ የሚቀሰቅሱ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ይቅርና በተደላደለ ህይወት ላይ እንኩዋን ቢገኝ ነጻነቱን ተገፎ ለመኖር ፈቃደኛ የለም፣ እናም አመጽ መነሳቱ አይቀሬ ነው ብለዋል::

ማድሰን በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው የኢትዮጵያው አምባገነናዊ አገዛዝ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ እንዳለበትና ይህን ለጊዜው አፍኖ እንደሚገኝ ነገር ግን ይህ አፈና የትም እንደማያደርስና የህዝብም ቁጣ ገንፍሎ አመጹ መነሳቱ እንደማይቀር ገልጸዋል::

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በገፍ የፓርቲው አባል የማድረግ ዘመቻ ሊጀምር ነው

የአምባገነኑን አገዛዝ ምንጮችን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ባወጣው ዘገባ አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስልጠና በሚል ሽፋን በርካታ ኢትዮጵያዊያንን የአገዛዙ ፓርቲ አባል የማድረግ ዘመቻ ሊጀምር እንደሆነ በየካቲት 8 ቀን የዜና እወጃ ፕሮግራሙ አስታውቆአል።

ኢሳት የውስጥ ዜና ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ እንደገለፀው ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስልጠና የተባለው አዲስ ዘመቻ አላማው ህብረተሰቡን የፖለቲካ ትምህርት በማስተማር የኢሃዴግ አባል የማድረግ ዕቅድ ነው። ከጊዜ ወደጊዜ እያየለ የመጣውን ህዝባዊ ተቃውሞና ጥላቻ ለማብረድ ወያኔ የተለያየ ጥገናዊ ለውጥ ለማካሄድ የሞከረ ቢሆንም ፤ ልማት እና ዕድገት በአገሪቱ አምጥቻለሁ የሚለው ባዶ ፕሮፖጋንዳ የአለም አቀፉ ህብረተሰብ በሰጠው የገንዘብ ድጋፍና እርዳታ በተሰሩ መንገዶች ርዝመት ወይም ባለሥልጣኖቹ ከደሃው ህዝብ ጉሮሮ በተነጠቀ የዘረፋ ገንዘብ እያሰሩ በሚያከራዩዋቸው ዘመናዊ ህንጻዎች ብዛት እና ቁመት ተለክቶ ህብረተሰቡን ሊያስደስት እንዳልቻለ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ መለስ ዜናዊንና ጥቂት ተከታዮቹን እያስጨነቀ እንደመጣ ለማወቅ ተችሎአል። ከዚህም በተጨማሪ የአገሪቱን ዘነች እትብታቸው ከተቀበረበት መሬት እና ቀዬ እያፈናቀሉ ለሼሽያ ከበርተዎችና ለአረብ ነጋደዎች በርካሽ ዋጋ እየተቸበቸበ ባለው መሬት ተጠቃሚ የሆኑት የህወሃት ሹመኞችና የክልል ወከሎቻቸው ድርጊት ህዝቡን እጅግ እያስመረረ በመምጣቱ የተከማቸው ህዝባዊ ብሶት መቸ እና የት ቦታ አስቀድሞ እንደሚፈነዳ ባለመታወቁ በወያኔዎች ሠፈር ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤ ፈጥሮአል ተብሏል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሊቢያ፣ ባህሬይን፣ ኢራን፣ የመንና ዮርዳኖስ ህዝቦች አመጽ ወደከፋ ደረጃ እየተሸጋገረ መሆኑ ታወቀ

በቱኒዚያ እንዲሁም በግብጽ "ዕምቢ ለነፃነቴ" ብሎ የተነሳው ህዝብ በተለይም ወጣቱ ክፍል መቋሚያና መቀመጫ ያሳጣቸው ቤን አሊና ሆስኒ ሙባረክ ሥልጣናቸውን ጥለው ከፈረጠጡ በሁዋላ ተመሳሳይ የሆኑ ህዝባዊ አመጾች በበርካታ ሃገራት በፍጥነት በመዛመት ላይ ሲሆን በሊቢያ፣ ባህሬይን፣ ኢራን፣ የመንና ዮርዳኖስ ህዝቡ የየሃገራቱን ቁንጮዎች በቃችሁን በማለት የተቃውሞ ሰልፎች በማደረግ ላይ ይገኛል:: ለአመታት የጥቂት ሥልጣን ጥመኞች መሣሪያ በመሆን ያገለገሉ በየአገሩ ያሉ ፖሊሲና ፀጥታ ሃይል ሠራተኞች ከሰላማዊ ሠልፈኞቹ ጋር መጋጨቱን በተቻላቸው መጠን እየሰወገዱ መሆኑን የተለያዩ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በመዘገብ ላይ ናቸው።

ኢራን ውስጥ ቀደም ብሎ ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይደረግ ተከልክሎ የነበረ መሆኑ ቢታወቅም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢራናዊያን እገዳውን በመጣስ ተቃውሞዋቸውን በማሰማት ላይ እንደሚገኙ ታውቁአል ። በኢራን በተደረገው ሰላማዊ ሠልፍ ፖሊስ ከሰልፈኞቹ ጋር ተጋጭቶ አንድ ሰላማዊ ሰው እንደሞተና አንዳንዶችም እንደቆሰሉ ተዘገቦአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መለስ እና ግብረ አበሮቹ አደረግን ያሉት የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ ማስተካከያ እንደገና ሊጨመር ነው ተባለ

የህዝብ ተቃውሞ ካሁን አሁን ተነሳብኝ እያለ በመባነን ላይ የሚገኘው ዘረኛው የመለስ አምባገነን አገዛዝ ባለፈው ወር የሸቀጦችን ዋጋ ውድነት ለማርገብ በሚል ሰበብ ያወጣው የዕቃዎች ዋጋ ተመን በገቢያ ላይ ከፍተኛ የሸቀጦች እጥረትን የፈጠረ መሆኑ ሲታወቅ ለደረሰው ውድቀት ከአገዛዙ የንግድ ድርጅቶች ጋር ምንም ትስሥር የሌላቸውን ነጋዴዎች ተጠያቂ ለማድረግ በከንቱ ሲዳክር ከሰነበተ ቦኋላ እንደገና የዋጋ ጭማሪ ሊያደርግ በዝግጅት ላይ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

አሁን ሊደረግ የታሰበው የዋጋ ማስተካከያ አገዛዙ ከነጋዴው ህብረተሰብ የደረሰበትን ጥላቻና ተቃውሞ ለማለሳለስ ነው የሚሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ቀደም ሲል ወጥቶ የነበረው የዋጋ ተመን ቸርቻሪ ነጋደዎች ምርቱን ከጅምላ ሻጮች ከሚገዙበት ያነሰ እንደነበር በመታወቁ ስህተቱን ላለመድገም እንዲመስል በተለያየ የንግድ ዘርፍ ለተሰማሩ ነጋዴዎች ለይስሙላ ያህል ሸቀጣ ሸቀጦችን የምትገዙበትና የምትሸጡበትን የዋጋ ዝርዝር ላኩልን በማለት እያወከቡዋቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል ። ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ የኢኮኖሚክስ ሙህር ችግሩ መሪ ነን የሚሉት ወይ የኢኮኖሚው ስሌት አልገባቸውም ወይም ደግሞ እንደለመዱት ሆን ብለው በህዝቡና በነጋደው ማህበረሰብ መካከል ከፍፍል ለመፍጠር የሚያደርጉት እርምጃ ነው በማለት የችግሩ መሰረት የአመታት የተሳሳተ የፖሊሲ ውጤት እና የመልካም አስተዳደር ጉድለት እንደሆነ ተናግረዋል። ወያኔዎች የገቢያ ንግድ ሚዛን ማንም በድንገት ተነስቶ ምርቶች በዚህ ዋጋ ይሸጡ በማለት በሚሰጠው ት ዕዛዝ ወይም አዋጅ የሚመራ ሳይሆን የምርትና አቅርቦት መመጣጠን የሚፈጥረው መሆኑን 20 አመት ሥልጣን ላይ ከቆዩ ቡኋላም ቢሆን አልተረዱትም በማለት የአምባገነኑ አገዛዝ ሰሞኑን በመውሰድ ላይ ያሉውን እርምጃ አጣጥለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሽብር ላይ ነው፣ የደመነፍስ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆኑ ተዘገበ

በቱኒሲያው የተጀመረውና ቀጥሎም ወደግብጽ እንዲሁም ወደተለያዩ ሀገራት እንደሰደድ እሳት እየተስፋፋ የመጣው የህዝብ አመጽ በዘረኛው አምባገነን መለስና ግብረ አባሮቹ ዘንድ ከፍተኛ ፍርሀትን መፍጠሩ በዚህም ምክንያት በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ከደህንነት ሰራተኞቹ ፡ ከወታደሮቹና ከተለጣፊ ፓርቲ መሪ ነን ከሚሉ ባንዳዎች ጋር ምክክር ሲያደርግ የሰነበተ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ባለፉት ሳምንታት ሴቶችንና ወጣቶችን በማሰባሰብ አገዛዙን እንዲደግፉ ለዚህም ተግባራቸው እነሱን በማደራጀት የገንዘብና የቦታ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው በመግለጽ ሲማጸን ሰንብቷል:: ይሁን እንጂ ሙከራቸው ያልተሳካላቸው የአምባገነኑ አገዛዝ የቀበሌ ካድሬዎች ከፌዴራል ፖሊስ ጋር በመጣመርና በየቤቱ በመዞር ወጣቶቹ በግድ እንዲፈርሙ መደረጋቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

ይህም አልበቃ ያለውና የህዝቡ ትግል ዛሬ ነገ ይነሳል እያለ በመባነን ላይ ያለው ወያኔ የተለመዱ የማስፈራሪያ ዘዴዎችን አጡዋጡፎ መቀጠሉን የአዲስ አበባ ዘጋቢያችን ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኦሮሚያ አንድ የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ባንዳ በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ታጣቂዎች እርምጃ የተወሰደበት መሆኑ ተዘገበ

ህብረተሰቡን በመከፋፈል ለረሀብ ለእስራትና ለግድያ እየዳረገው ያለው የአምባገነኑ መለስ ግፈኛ አገዛዝ እየፈጸመ ያለው ጭቆና ተባብሶ እንደቀጠለ በሚነገርበት ኦሮሚያ ወያኔዎች ጥቂት ሆድ አደር ባንዳዎችን በሃላፊነት ቦታ ላይ በማስቀመጥ በገዛ ወገናቸው ላይ ግፍ እንዲፈጽሙ ሲያደርጉ መቆየታቸው የሚታወቅ ሲሆን በምስራቅ ኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሃረርጌ ዞን የደህንነት ሃላፊ በመሆን በህዝቡ ላይ ይህ ነው የማይባል በደልና ስቃይ ሲፋጽም በነበረ አንድ የወያኔ ባለስልጣን ላይ የኦሮሞ ነጻነት ታጣቂ ቡድን እርምጃ እንደወሰደበት ለማወቅ ተችሎአል። በጉዳዩ ላይ ባካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ደስታቸውን እየገለጹ ሲሆን አምባገነኑ አገዛዝ ግን በጉዳዩ ላይ ምንም አስተያየት እንዳልሰጠ ለማወቅ ተችሎአል።

እንዲህ አይነቱ እርምጃ ለግል ጥቅም ሲሉ ከዘረኛው የመለስ አገዛዝ ጋር በማበር በገዛ ወገናቸው ላይ ለሚዘምቱ ባንዳዎች ጥሩ የመንቂያ ጥሪ ደወል መሆኑን የተናገሩ አንድ ለዘጋቢያችን አስተያየታቸውን የሰጡ የአዲስ አበባ ነዋሪ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ሰርጎ በመግባት ከፍፍል ለሚፈጥሩና መረጃ ለሚያቀብሉ ሆድ አደሮች መልካም ትምህርት ሊሆን ይገባል በማለት በድህረ ምርጫ 97 ህዝቡን ከደው ከወያኔ ጋር በመወገን የህዝብን ድል ያስቀለበሱትን አንዳንድ በስመ ተቃዋሚ ፓርቲ የሚንቀሳቀሱት ግለሰቦች ላይ ጣታቸውን ቀስረዋል። አያይዘውም ወያኔ የህዝባችን ቅስም ሰብሮ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# የኢትዮጵያ ወጣቶች ከቱኒዝያና ግብፅ እኩያዎቻቸው ሊማሯቸው የሚገቡ ቁምነገሮች

"በሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አብዮት ከሰሃራ በታች ወደ አሉ የአፍሪቃ አገሮች ይዳረሳል ወይስ አይዳረስም?" በሚል አፍሪካዊያን በየቦታው ክርክሮች ይዘዋል። ቤን ዓሊ ከቱኒዝያ እንደተባረረ ከፊል ግብፃዊያን ግብፅን ከቱኒዝያ የሚለዩዋት ነገሮች ላይ አጽንዖት እየሰጡ "ግብፅ ቱኒዝያ አይደለችምና እዚያ የሆነው እዚህ ሊደገም አይችልም" እያሉ ሲከራከሩ ነበር። እርግጥ ነው ግብፅ ቱኒዝያ አይደለችም፤ ነገር ግን ቱኒዝያ የሆነው እግብፅም ተደገመ። ህዝባዊው ቁጣ ግብፅ ውስጥ አላበቃም። "ትናንት ሙባረክ፤ ዛሬ አብደላ!!!" የሚሉ መፈክሮች በችጋር በተጎዳችው፤ ውስጣዊ አንድነት በሌላት እና በኢንተርኔት ስርጭትም እጅግ ኋላቀር በሆነችው የመን ውስጥ ተፋፍሟል። በአንፃሩ ደግሞ የኑሮም ሆነ የሥራ አጥነት ችግር እጅግም ያላጠቃትን ባህሬንን አልማራትም። ከአመት በፊት በምርጫ ሰበብ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ አመጽ በጉልበት በታፈነባት ኢራን ውስጥም አዲሱ አብዮት እግሩን አስገብቷል። ባጭሩ ይህ በዓይነቱ አዲስ የሆነው ህዝባዊ ቁጣ እጅግ በተለያዩ የኑሮና የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃዎች ላይ ወደአሉ አገሮች ተዳርሷል።

ስለሆነም ኢትዮጵያ ቱኒዝያ ወይም ግብፅ አለመሆኗ ወይም በአንዳንድ አመላካከቶች እነሱን አለመምሰሏ እዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አብዮት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይዘልቅ ይከለክለዋል ማለት አይደለም። በዚህም ምክንያት "እኛ ዘንድ ይደርሳል፤ አይደርስም?" በሚል ከመከራከር "ከእነዚህ አገራት ህዝባዊ አብዮቶች የምንማራቸው ቁም ነገሮች ምንድናቸው?" ብሎ መጠየቅና የጎደሉንን አሟልቶ መገኘት ከፍተኛ የሆነ ተግባራዊ ፋይዳ ያለው ጉዳይ ነው ።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ከቱኒዝያና ግብፅ የእድሜ አቻዎቻቸው በርካታ ነገሮችን መማር ይችላሉ ብለን እናምናለን። በተለይ ደግሞ ወጣቶቻችን የሚከተሉት ነጥቦችን እንዲያጤኑ እንመክራለን።

1. ድርጅት፤ አምባገነንነት በሰፈነባቸው አገሮች የዘመኑ ወጣቶች የሚፈጥሯቸው ድርጅቶች ቀድሞ ከምናውቃቸው የድርጅት ዓይነቶች በእጅጉ የተለዩ ናቸው። የቱኒዝያም ሆነ የግብጽ ወጣቶች ራሳቸውን በጥሩ ሁኔታ ያደራጁ ቢሆንም እንኳን ድርጅቶቻቸው በልማድ የምናውቃቸው ዓይነት ግትር መዋቅር ያላቸው አይደሉም። ድርጅቶቻቸው በኦፊሴል ያልተመዘገቡ፤ እየታዩ የማይጨበጡ ዓይነት ሊ ንፎርማል ስብስቦች ናቸው። እነዚህ ስብስቦች የሥራ ቡድኖች በመሆናቸው እንደ ሥራው ብዛትና ማነስ በቀላሉ የሚሰፉና የሚጠቡ ናቸው። እነዚህ የወጣቶች ድርጅቶች በተለያየ ጊዜዓት የተለያዩ ቅርጾችን ይዘዋል። አንዳንዶቹ በአካል የማይተዋወቁ የፌስ ቡክ ጓደኞች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ደግሞ የኳስ አድናቂዎች ናቸው። ቱኒዚያዊያንና ግብፆች በእንዲህ አይነቱ ተጣጣፊ አደረጃጀት የመንግሥት ሰላዮችን ጭንቅላት አዙረዋል። የኢትዮጵያም ወጣቶች ከቱኒዚያና ግብጽ ወጣቶች በመማር ከኢትዮጵያ ባህልና እድገት ጋር ተስማሚ የሆነ ሆኖም ተጣጣፊ የሆነ አደረጃጀት ሊከተሉ ይገባል።

2. **የመረጃ ልውውጥ፤** በወያኔ ደባ ምክንያት ኢትዮጵያ አገራችን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እጅግ ወደ ኋላ የቀረች ቢሆንም ወጣቱ ልዩ ልዩ የፈጠራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የመረጃ መረቡን ማስፋት፤ ዘመናዊውንም ባህላዊውንም የመረጃ ልውውጥ አቀናጅቶ መጠቀም ይኖርበታል። ለምሳሌ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት የሚተላለፉ ለእውነት ወገንተኛ የሆኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ስርጭቶች በኢትዮጵያ በስፋት እንዲታዩ ዘመቻ በማድረግ የመረጃ አድማስን ማስፋት ይቻላል። ለእነዚህ ሬድዮዎችና ቴሌቪዥኖች መረጃዎችን በመስጠትም የጠበቀ ግኑኝነት መፍጠር ይገባል። ወጣቱ የማያልቅ የፈጠራ ክህሎቱን ለመረጃ ልውውጥ ማዋል ይኖርበታል።

3. **መቻቻል፤** ሰዎች ለትላልቅ ዓላማዎች ሲሰለፉ መለስተኛ ቅራኔዎች ፋይዳ አይኖራቸውም። የነፃነት ትግል ግብፃዊያንን አፋቅሯል። በክርስቲያኖች ጥበቃ ሞስሊሞች ሲሰግዱ፤ ለክርስትያኖች ቅዳሴ ሞስሎሞች ከለላ ሲሰጡ ማየት ችለናል። የሁለቱም ሃይማኖቶች ተከታዮች በጋራ በየእምነቶቻቸው ለነፃነት ፀልየዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ከዚህ ጠቃሚ ትምህርት ሊቀስሙ ይገባል። የነፃነት ትግል ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታና እድሜ አይለይም። ነፃነት ሰው በሰውነቱ ብቻ ሊያገኘው የሚገባ ፀጋ ነው። ሆኖም ግን በግብጽ ሙባረክ እንደሞከረው፤ በየመን አሊ አብደላ ሳለህ እንዳደረገው ሁሉ ወያኔም ህዝብን ከህዝብ በጎዳና ለማጣላት እና እሱ ገላጋይ ሆኖ ለመግባት መሞከሩ አይቀርም። ወጣቶች ይህን ቀዳዳ በተቻለ መጠን ማጥበብ ይኖርባቸዋል። ለዚህ አንዱ መፍትሄ የተቃውሞ ዓላማን ግልጽ ማድረግ ነው። ዳቦ፣ ሥራ፣ ፍትህና ነፃነት ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታና እድሜን አይለዩም።

4. **በራስ የመተማመን ስሜት:** ቱኒዚያዊያንና ግብፃዊያን ፍርሃትን ማሸነፍ የቻሉ በራስ የመተማመን ስሜት በመፍጠራቸው ነው። ግብፅ መለዮ ለባሽ ከሆነው የጦርና የፓሊስ ሠራዊት ውጭ 350 000 የሚደርስ ሰላይና ነጭ ለባሽ አላት ተብሎ ይገመታል። ይህ ሁሉ ሠራዊት ግን አመጹ እንዳይነሳ ማገድ፤ ከተነሳም በኋላ ማፈን አልቻለም። በራስ የመተማመን ስሜት መተሳሰብን፣ መተጋገዝን፣ የጋራ ጥቅምን ማስቀደምን ይፈጥራል። ወጣቱ በራሱ ሲተማመን ከታላላቆቹ "አመራር" መጠበቅ ይተዋል። ያኔ ነው እውነተኛ ህዝባዊ አብዮት ማካሄድ የሚቻለው።

5. **ሙብት፣ ክብር እና ባለቤትነት:** በቱኒዝያና ግብፅ ሰብዓዊ መብቶች፣ ሰብዓዊና አገራዊ ክብር እና የሃገር ባለቤትነት ጉዳይ በስፋት የተነሱ ፍሬ ሃሳቦች ናቸው። አገራችን በሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ዓለምን ትመራለች። አገራችን ፓሊስ ወንዶችን የዘር ፍሬ፤ የሴቶችን ደግሞ ጡት በመቀጥቀጥ የሚደሰትባት አገር ናት። እንዲህ ዓይነቱ አረመኔያዊ ተግባር የሚፈጸመው ደግሞ ሩቅ ሳይሆን በዋናው ከተማ አዲስ አበባ ውስጥም ነው። በአንድ ወቅት የጀኖሳይድ ዎች ፕሬዚዳንት ዶ/ር ግሪጎሪ ስታንተን እንደተናገሩት አገራችን በአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ውስጥ ትገኛለች። በአንድ ትንሽ ቡድን ቅኝ የመገዛትን ያህል አዋራጅ ነገር የለም። ወጣቱ ከዚህ ውርደት ራሱን ነፃ አውጥቶ የራሱን ክብር ለማስጠበቅ መነሳት ይኖርበታል። ወጣቱ "ኢትዮጵያ የኔ ናት!" ብሎ እንዲነሳም ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ወጣት እነዚህ አምስት ነገሮች ከሰሜን አፍሪቃ አቻዎቹ መማር አለበት ብለን እናምናለን። ጊዜ የለም። ሁኔታዎች በፍጥነት እየተቀያየሩ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ወጣት ለመብቱ፤ ለክብሩና ለሃገሩ ሲል ዛሬውኑ ይነሳ!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከ1997 ምርጫ በፊት ወደ ሶስት መቶ ሺ ይገመት የነበረውን የአገዛዙ ፓርቲ አባላት በድህረ ምርጫ ሰሞን በደረሰበት ቀውስ ቁጥርን በድንገት ከአምስት ሚሊዮን በላይ አድርሶት እንደነበር የሚያስታውሱት ምንጮች የቁጥሩ መብዛት ለወያኔ ካስገኘው ጠቀሜታ ይልቅ ይዞበት የመጣው ዕዳ እንደሚበዛ ይናገራሉ። በሥራ ዋስትና ለትምህርት ዕድል ወይም ለተለያየ የኢኮኖሚ ጥቅማ ጥቅሞች ወያኔ የተቀላቀሉ ሁሉ በወገኖቻቸው ላይ የሚፈጸመውን በደልና መከራ ለመገንዘብ ከማንም በላይ የቀረቡ እንደመሆናቸው ህዝባዊ ተቃውሞ የተቀሰቀሰ ዕለት ለነጻነታቸው ሲሉ በወያኔ ላይ ከንዳቸውን ከሚያዞሩት የመጀመሪያው እንደሚሆኑ ቅርብ የተባሉት ካድሬዎች በየመንደሩ እያሰሙት ካለው የመረረ ብሶት መረዳት ይቻላል ተብሎአል። ወያኔ አሁን እያዘጋጀው ያለው የጎልማሶች ሥልጠና የደረሰበትን ቀውስ የሚያረግብ ሳይሆን የህወሃት አመራር ግራ መጋባትን ብቻ የሚያመለክት ነው

## አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሽብር ላይ

... (ከገጽ 1 የዞረ)

ሰሞኑን በየቀበሌው ወላጆችን በመጥራት ልጆቻቸው በምንም አይነት ተቃውሞ ላይ ቢገኙ ለሚደርስባቸው አደጋ ተጠያቂ አይደለንም እያሉ ያስፈራሩ መሆኑ ሲታወቅ በተለያዩ የነጻው ፕሬስ ላይ ለተሰማሩን ለህዝቡ ነጻና ገለልተኛ መረጃ በማቅረብ የሚታወቁ አሉ የሚባሉ ጥቂት ጋዜጦችን እና የጋዜጣ አዘጋጆችን በከፍተኛ ሁኔታ ላይ በማስፈራራት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል። ከነዚህም ወስጥ ሰሞኑን በሰሜን አፍሪካ በተነሳት ህዝባዊ አብዮት ዙሪያ በተደጋጋሚ ይጽፍ የነበረው እስክንድር ነጋን ባለፈው ሳምንት ከኢንተርነት ካፌ ቤት ሲወጣ በወያኔ የደህንነት ሰራተኞች ታፍኖ ወደ ፌደራል ማእከላዊ ፖሊስ ጽ/ቤት የተወሰደ ሲሆን በዚያም የነመለስ ጋሻ ጃግሬዎች ምንም አይነት ህዝብ ሊያነሳሳ የሚችል ጽሁፍ እንዳይጽፍ ያስጠነቀቁት ሲሆን ምንም አይነት ህዝባዊ አብዮ ቢካሄድ መጀመሪያ አንተ ጋ ነው የምንመጣው በማለት ከባድ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸው ታውቆአል። አቶ እስክንደር ነጋ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ በወያኔ ገዢዎህ ለስር እና ሰቆቃ መዳረጉ ይታወሳል።

በተያያዘ ዜና የዘረኛው አገዛዝ በተደጋጋሚ የሚዲያ ዘመቻ ከፍቶብናል በማለት ሲኮንነው የነበረውንና ህዝብን ለአመጽ ያነሳሳል የሚለውን የኢትዮጵያ ሳተላይ ቴሌቪዥን ስርጭትን ለማቋዋረጥ ብዙ ሙከራ ቢያደርጉም ለተወሰኑ ሰአታት ስርጭቱ ተቋርጦ የነበረው ኢሳት በ 24 ሰአት ውስጥ ተመልሶ አየር ላይ መዋሉ እጅጉን ያበሳጫቸው መሆኑ ለማወቅ ተችሎአል።

ይህ ሁሉ ርበርብ እንመለስ ለህዝቡ ያላቸውን ከፍተኛ ንቀት የሚያሳዩ ሲሆን ህዝቡ ከነሱ ምን ያህል ርቆ እንደሄደ በቅጡ የተረዱት አይመስለኝም ያሉት አንድ ዘጋቢያችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝ ይህ ለሁለት አስርት አመታት ሰረገኖና ሲመዘበር የኖረ ህዝብ ብሶቱ ፈንድቶ ሲወጣ ማቆሚያ እንደሌለውና ውጤቱም እስከምን ድረስ እንደሚሄድ በቱኒሲያና በግብጽ አይተናል ብለዋል ። ቀጥለውም ስለዚህም ወያኔዎች እየወሰዱት ያሉት እርምጃዎች በራሳቸው ላይ ነገሩን ያከብደዋል እንጂ ህዝቡን ከትግል ያቆመዋል ብለው ማሰባቸው እብደት ነው፡ ህዝቡማ በሚያዚያ30 1997 ላይ ባደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ለነሱ ያለውን ጥላቻ በግልጽ አሳይቶአል በማለት ሃሳባቸውን አጥናቀዋል።

## በኦሮሚያ አንድ የዘረኛው አምባገነን

... (ከገጽ 1 የዞረ)

ስልጣን ላይ የቆየው ከበረሃ ይዞ በመጣ ተጋዳላዮቹ ጥንካሬና ብልህነት ሳይሆን ለጥቃቅን ጥቅሞች የህዝባቸውንና የአገራቸውን የወደፊት ህይወት በሸጡ ለራሳቸው ስብ ዕናም ሆነ ለነጻነታቸው ምንም ክብር በሌላቸው ሰው መሳይ እንስሶች ነው ብለዋል። የአካባ ታጣቂዎች በ እንደዚህ አይነቶቹ ሚፈሪያ ዘንች ላይ የወሰዱት እርምጃ ሊቀጥል እና በሌሎቹ ክልሎችም ሊበረታታ ይገባል ያሉ ሌላ አስተያየት ሰጭ ደግሞ የአገርን ሃብት ተቫርኮ ለመመዝበርና በአቋራጭ ለመክበር ባለው ፍላጎት ከአምባገነኖቹ ጉያ ሥር ተወሽቆ ለሚሠራው ወንጀል ተባባሪ መሆን ዛሬ ከጥቃት ሁሉ የሚከለል መሸሸጊያ ተደርጎ የሚቆጠረው ዘረኛ አምባገነን ሲወድቅ ከህዝብ ፍርድ ሊያመልጡ እንደማይችሉ ሰሞን በቱኒዚያና በግብጽ አምባገነኖችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ላይ እየደረሰ ካለው ውድቀት ሊማሩ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ነጻነት ታጣቂዎች ከዚህ ቀደምም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ለወያኔ ባንዳ በመሆን በገዛ ህዝባቸው ላይ በደልና ጭቆና ፈጽመዋል የተባሉ ባለስልጣናትን ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሩ እርምጃ በመውሰድ ለህዝቡ እረፍት ሲሰጥ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ግንቦት7ስ በምን ይለያል?

(ዶ/ር ታደሰ ብሩ) ክፍል 2 የመጨረሻ ክፍል

**2. የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነትን በተመለከተ**

የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነቶች የቅራኔዎች ምንጭ የሚሆኑባቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ሶስቱን ብቻ ልጥቀስ

**2.1 የጌታና ሎሌ ግኑኝነት**

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እንደምን አምባገነንነትን "እንደተለማመደ" ዳዊት ወልደጊዮርጊስ የሚከተለውን በመሰለ አገላለጽ አብራርቶልናል።

*በመጀመሪያ እሱም ሻለቃ እኛም ሻለቃ ነንና እጃችንን እኪሳችን ዉስጥ ከተን እናወራ ነበር። ሳናውቀው እጃችን ከኪሳችን ወጣ። አሁንም ሳናውቀው እጃችን ወደኋላ ዞረ። ሳናውቀው "ጓድነትዎ" ማለት ጀመርን .... እሱ ምንያድርግ?*

በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች ውስጥ የአባላት እኩልነት በወረቅትና በወሬ ብቻ ነው ያለው። ግኑኝነቶች በአመዛኙ የጌታና የሎሌ አይነት ናቸው። ስለዚህ በአንድ በኩል ጌቶችና ታማኝ ጋሻ ጃግሬዎች፤ በሌላ በኩል ደግሞ አማጺያንና አልቃሾች ተፋጠዋል።

**2.2 ዘረኝነት**

ዘረኝነት የወያኔና ሌሎች በዘር የተደራጁ ድርጅቶች ችግር ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ዘረኝነት ህብረብሄራዊ ነን የሚሉ ፓርቲዎችም ችግር ነው። ብዙ ፓርቲዎች በጣም ረቂቅ በሆነው የዘር የውስጥ ፓለቲካ ምክንያት ተተኪ መሪዎችን ማፍራት አልቻሉም።

**2.3 የመሪዎች ፉክክር**

አንዳንድ ድርጅቶች በይፋ ከሚታወቀው መሪ በተጨማሪ ሌላ በይፋ የማይታይ መሪ አላቸው። ሁለቱ መሪዎች ተፎካካሪ ከሆኑ ሁለት የንብ አወራዎች በአንድ ቀፎ ውስጥ መኖር እንደማይችሉ ሁሉ እነሱም ድርጅቱን በትነው የየድርሻቸውን ይዘው ሊጓዙ ይችላሉ። ሁለቱ መሪዎች ተደጋጋፊ ከሆኑና በይፋ የማይታወቀው መሪ በይፋ ከሚታወቀው መሪ በላይ ተሰሚነት ያለው ከሆነም ድርጅቱ ለቅራኔ ቅርብ ነው።

**3. የድርጅቱ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ በተመለከቱ የሚነሱ ቅራኔዎች**

ግልጽ የሆነ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ አለማስቀመጥ ድርጅትን የንትርክ ቤት ያደርጋል። አንዳንድ ድርጅቶች ምን እንደሚፈልጉ በውል ሳያውቁ ሲቀር ይህንን ድክመታቸውን የሚሸፍኑት አባሎቻቸውን ስሜታዊ በሆነ እምነት በማጥመቅ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት ብዙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ማርክሲዝም፣ ሌኒኒሊዝም፣ ማኦኢዝምን ለዚህ ዓላማ ተጠቅመዋል። እነዚህ እምነቶች ለጥያቄዎች ሁሉ የማያወላዳ ምላሽ ስላላቸው "ወደፊት ምን ዓይነት ኢትዮጵያን መፍጠር እንፈልጋለን?" በሚለው ጥያቄ ራሳቸውን ማስጨነቅ አላስፈለጋቸውም። በወቅቱ ከነበሩት ድርጅቶች ወያኔ በእጅጉ ይለያል። ወያኔ የአማራ ጥላቻ (በተለይም የሸዋ አማራ ጥላቻ) የእምነቱ ምሰሶ አድርጎ ነው የተነሳው። እርግጥ ነው እሱም እንደ ሌሎቹ ማኦኢዝምና ስታሊኒዝም ሰብኳል፤ አሁን ደግሞ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ልማታዊ መንግሥት ስለሚባሉ ነገሮች ያነበንባል። ይሁን እንጂ እነዚህን ለሕዝብ ግኑኝነት ሥራዎች የሚገለገልባቸው ጭምብሎቹ ናቸው። ወያኔ ትንሽ ችግር ውስጥ በገባ ቁጥር ጭንብሉን አሽቀንጥሮ ወደ ትምክህተኛ አማራ ትንታኔው ይመለሳል። ለምሳሌ ሰሞኑን እነስዬ አብርሃን የሸዋ አማራ ቅጥረኞች በማለት የሚኮንኑው ጽሁፍ አይጋ ፎረም ላይ ታገኛላችሁ። እሱ ነው የወያኔ ዋነኛ አቋም ማለት። የመለስም ዜናዊ የመቀሌ ንግግሩ መሠረትም ይኸው ነው።

ሌሎችም በርካታ የኢትዮጵያ የፓለቲካ ስብስቦች የርዕይ ቀውስ ሲገጥማቸው ብሶትን መቀስቀስ አማራጫቸው ይሆናል። አክራሪ እምነቶችም የርዕይ ቀውስ መሸፈኛነት የሚውሉበት አደጋም አለ። ይህ አካሄድ ስሜታዊ ከመሆኑ በላይ የሚቀሰቅሰው የድርጅት ውስጥ ቅራኔ እጅግ አደገኛ ነው።

**4. የድርጅት ደንቦችና መመሪያዎች እና አፈፃፀማቸው**

በድርጅቶች ውስጥ የሚነሱ ቅራኔዎች ከድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተዛምዶ አላቸው። በአንድ በኩል ደንቦች ራሳቸው የቅራኔ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ አባላት አንድን ደንብ በማጽደቅና ባለማጽደቅ ሊጣሉ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ተደንግጎ ተቀባይነት ያገኘ ደንብም የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ "ደንብ ጥሳችኋል"፤ "የለም እኛ አይደለንም እናንተ ናችሁ የጣሳችሁት" በመባባል እንደሚበጣበጡት ማለት ነው። ቅራኔ ውስጥ የገቡ አንጃዎች የድርጅቱን ደንብ ማጣቀሳቸው መቼም የማይቀር ነው። ደንቦች ሥርዓት ማስያዣ መሆን ሲገባቸው የቅራኔ ምንጭ የሚሆኑበት አጋጣሚ በርካታ ነው።

**5. የውጭ ግኑኝነትን በተመለከተ**

አንዳንድ ድርጅቶች ወዳጅና ተፎካካሪዎቻቸውን ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላሉ። ወዳጅ ከሚሏቸውም ጋር የትብብራቸው መጠን እስከምን ድረስ እንደሆነ በግልጽ የተወሰነ ጉዳይ ስለሌለ እከሌን ከሚባለው ድርጅት ጋር ተባብረን መሥራት አለብን ወይስ የለብንም የሚያስነሳው ጠብ ድርጅትን እስከማፍረስ ሊያደርስ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ድርጅቶች በስውርም ሆነ በግልጽ በሚያደርጉት ጣልቃገብነት አንድ ድርጅት ሊበጠበጥ ይችላል። ይህ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተለመደ ነው። ድርጅቶችን በማበጣበጥ ወያኔን የሚያህል እስካሁን የለም።

ክብራትና ክቡራን

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወደፊት መናጥ ከደረሰበት በክብርና ሞገስ ለመፍታት የመጀሪያው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ግንቦት 7 እንዲህ ዓይነት ወቅት ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ በማወቅ እራሱን እያዘጋጀ ያለ ድርጅት ነው። ከሁሉ አስቀድሞ አፍራሽ የሆኑ የተካረሩ ቅራኔዎች እንዳይፈጠሩ የመከላከያ ዘዴዎችን ቀይሶ በሥራ በማዋል ላይ ያለ፤ ዘመናዊ አደረጃጀቶችን ለመማር ፈቃደኛ የሆነ ድርጅት ነው። ይህ የዛሬ ውይይትም የዚህ አመላካች ነው።

ከላይ የዘረዘርኳቸው (1) የአባላት ተክለሰውነት፣ (2) የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነት፣ (3) የድርጅቱ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች፣ (4) የድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች እና አፈፃፀማቸው፣ እና (5) የድርጅቱ የውጭ ግኑኝነት ተግባራት አንድን ድርጅት ችግር ውስጥ ሊጥሉ የሚችሉ ቅራኔዎች መመንጫ አካላት ናቸው። እነዚህ ጉዞ ከመጀመሩ በፊትና በጉዞም ተደጋግመው ሊፈተሹ እንደሚገቡ የመኪና አካላት ለምሳሌ ጎማ፣ ፍሬቻ፣ መብራት፣ ፍሬን፣ የዘይት መርጫ፣ የነዳጅ ማስተላለፊያ እና የመሳሰሉትን አድርገን እንያቸው። ከእነዚህ ውስጥ የአንዳቸው መሰናከል ጉዞውን ሊያስተጎጉል እና የአደጋውን መጠን ሊያበዛው ይችላል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን በቅድሚያ አውቆ እየተንቀሳቀሰ ያለ ድርጅት ነው።

ግንቦት 7 ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያስችለውን ድርጅታዊ ጥንካሬ በምርምሮች በታገዘ መንገድ መገንባት ይኖርበታል። ለዚህም እያንዳንዱ የግንቦት7 ሕዋስ ቅራኔዎችን በአግባቡ ማኔጅ የሚያደርግበትን ክህሎት ሊያዳብር ይገባል። እያንዳንዱ ሕዋስ ራሱን የሚከተሉትንና መሰል ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርበታል።

- በሕዋሳችን አብሮ የመጓዝ ችግር ያለበት ማነው? ችግሩ ከምን የመነጨ ነው?
- የትኞቹ ነገረ ጉዳዮች /issues/ ግልጽ አይደሉም?
- የትኞቹ ነገረ ጉዳዮች ቅሬታን ይፈጥራሉ?
- ሕዋሳችን በአሁኑ ሰዓት እምን ደረጃ ላይ ነው ያለው?
- ሕዋሳችንን ለቅራኔ የሚያጋልጡ ጉዳዮች አሉ ወይ?
- በአባላት የግል ፍላጎትና በጋራ ፍላጎቶቻችን መካከል ያለውን ተቃርኖ እንዴት ልንፈታ እንችላለን?
- አምስቱ ቦታዎች ላይ ትኩረት ሰጥተን መከላከያ አበጅተናል?
- እያንዳንዱ አባል ምን ያህል ጊዜና ጉልበት በቡድን ሥራ ላይ ያውላል?
- የእያንዳንዱን አባል የግል ችሎታና ፈጠራ በአግባቡ ተጠቅመንበታል ወይ?

የግንቦት 7 ሕዋሳት ሰፋ ያለ ነፃነት ያላቸው አሃዶች ናቸው። ሕዋሳቱ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሲወጡ እና አፍራሽ ለሆኑ ቅራኔዎች የማይመቹ፤ ተግባር ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ መላው ንቅናቄዓችን በአስተማማኝ መለዋወጫዎች የተገነባ መኪና እናደርገዋለን።

በዚህም መሠረት ንቅናቄዓችን ከሕዋሶቹ ጀምሮ ራሱን ከአፍራሽ ቅራኔዎች የሚከላከልበት ሥርዓት እያበጀ ነው።

1. የአባላት ተክለሰውነት ተመርኩዘው ሊመጡ የሚችሉ ቅራኔዎችን ለመከላከል ድርጅታችንንና ራሳችንንም የእድሜ ልክ ተማሪዎች በማድረግ ዘወትር ግንዛቤዓችንና ክሎቶቻችንን ለማዳበር እንጥራለን። የተዛቡ ግንዛቤዎች እንዳይኖሩን ደግሞ ህይወት ያለው ውይይት የምናካሄድባቸው መድረኮችን ለማቋቋም ጥረት እያደረግን ነው።
2. የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነትን ተመርኩዘው ሊመጡ የሚችሉ ቅራኔዎችን ለመከላከል የአባላት ሥነምግባር መርሆዎች ወጥተው ተሰራጭተዋል። እነዚህ የሥነ ምግባር መርሆች በቅርቡ በታተመው መጽሃፍ ውስጥ ተካትተው አባሎቻችን ባልሆኑ ኢትዮጵያዊያንም እንዲታወቁ አድርገናል። የግንቦት7 አባላት በእነዚህ የሥነምግባር መርሆዎች የታነፁ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የግንቦት 7 አባል ከዘረኝነት የፀዳ መሆንና በዜጎች እኩልነት የሚያምን መሆን እንዳለበት በመርሆዎቹ ተደንግገዋል። በዚህም ምክንያት በአባላት ምልመላ ወቅት እነዚህ መርሆዎች ከመመዘኛዎቹ ዋነኞቹ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ግንቦት 7 እነዚህን እሴቶቹን ወደ ድርጅታዊ ባህል ደረጃ ለማሳደግ ጥረት ያደርጋል።
3. የንቅናቄዓችን ርዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች በተመለከቱ ቅራኔዎች እንዳይነሱ በማያሻማ ሁኔታ በመሥራች አባላት ውይይት ዳብረው በመላው አባላት ልቦና እንዲሰርፁ እየተደረገ ነው።

ለማስታወስ የግንቦት7 ርዕይ የሚከተለው ነው

*የግንቦት 7 ንቅናቄ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፣ የኢኮኖሚ ብልጽግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚያገኝበት፣ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።*

ተልዕኮው ደግሞ የሚከተለው ነው

*የግንቦት 7 ቀዳሚ ተልዕኮ የመንግሥትና የፓለቲካ ሥልጣን በሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደት የሚያዝበትንና የሃገሪቱ ዜጎች ምርጫ በተግባር የሚገለጽበትን ብሄራዊ ፓለቲካዊ ሥርዓት እንዲገነባ ማገዝ ነው።*

ይህን ተልዕኮ በደንብ የተገነዘ ሰው ግንቦት 7 በዓይነቱ ልዩ የሆነ የፓለቲካ ኃይል መሆኑ ይገነዛባል። ከሁሉም በላይ ግንቦት 7 የተቀቋመው የመንግሥትን ሥልጣን ይዞ ሕዝብን ለማስተዳደር አይደለም። በዚህም ምክንያት የኔ ፓሊሶች የተሻሉ ናቸው እያለ ብሎ ክርክር የሚገጥምበት ምክንያት የለም፤ ለዚህ የሚሆኑ ፓሊሲዎችም የሉትም። ግንቦት 7 የሚታገለው የመንግሥት ሥልጣን በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚያዝበትን ሥርዓት መገንባት ነው። የግንቦት 7 ተልዕኮ ኢትዮጵያን መምራት እንፈልጋለን የሚሉ ፓርቲዎች ፍላጎታቸውን በነፃነት ለሕዝብ ዳኝነት አቅርበው የሚመረጡት ሥርዓት ማቆም ነው።

ይህን ሥርዓት የማቆምን ትግል እኔ መምራት አለብን ወይም ኃላፊቱ የኔ ብቻ ነውም አላለም። ግንቦት 7 ተልዕኮውን ተግባራዊ የሚያደርገው ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንደሆነ ያምናል። ለዚህም ነው ተልዕኮው ይህንን የሕዝብን ትግል ማገዝ የሆነው።

በመጨረሻም ከሌሎች የፓለቲካ ፓርቲዎች በተለየ መንገድ ግንቦት 7 እንደ ፕሮጀክት የመጠናቀቂያ ጊዜ አለው። እንደ ፕሮጀክትም ውጤቱ በቀላሉ መለካት የሚችል ነው። ተልዕኮዓችንን አጠናቀቅን የምለው በዲሞክራሲያዊ ምርጫ የመጀመሪያው መንግሥት ተመርጦ ሥራውን የጀመረ እለት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የረዥምና የአጭር ጊዜዓት እቅዶችን አውጥተን መንቀሳቀስን እየተለማመድን ነው። በእቅድ መመራት ሥራን ከማቀላጠፍም ባሻገር አባላት በየጊዜው በሚቀያየሩ የፓለቲካ ንፋሶች ምክንያች ትኩረታቸው እንዳይዛነፍ ይረዳል ብለን እናምናለን።

4. የድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች አፈፃፀም በተመለከቱ ቅራኔዎች እንዳይነሱ የድርጅት ደንቦችና መመሪያዎች ከመውጣታቸው በፊት ግልጽና ሰፊ ድጋፍ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ሥራዎች ይደረጋሉ። ደንቦች ያለ አድልዎ ተፈፃሚ ይደረጋሉ።

   በዚህም ረገድ ሥራዎቻችንን በደንቦችና መመሪያች መሠረት ለመሥራት ጥረት እያደረግን ነው። ከስብሰባ ሰዓት አከባበር ጀምሮ እስከ ሪፖርቶችን በወቅቱ እስከማቅረብ እንዲሁን የአባልነት ግዴታዎችን በአግባቡ እስከመወጣት ድረስ ያሉት ጉዳዮችን ሥርዓት ለማስያዝ ጥረት እያደረግን ነው።
5. የድርጅቱ የውጭ ግኑኝነትንም በተመለከተ ግንቦት 7 ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለሚኖረው ግኑኝነት ግልጽ የሆነ መስፈርት አዘጋጅቷል።

ግንቦት 7

- የኢትዮጵያን ሉዓላዊ አንድነት፣
- የፖለቲካ ሥልጣን፣ በሃገር አቀፍ ይሁን ከዚያ በታች በሚገኙ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም?

... (ከገጽ 3 የዞረ)

አስተዳደራዊ አሃዶች ውስጥ የሚያዘው ዜጎች በእኩልነት በሚሰጡት የአንድ ሰው አንድ ድምጽ ሥርዓት መሆኑን፣ እና

- የትብብሩ የትግል ዓላማ ሥልጣን ለመያዝ ሳይሆን ሥልጣን በሕዝብ ፈቃድ የሚያዝበትን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለማመቻቸት መሆኑን ከተቀበሉ ኃይሎች ሁሉ ጋር ተባብሮ ለመሥራት ዝግጁ ነው።

ክብራትና ክቡራን

ለዘመናት ከኢትዮጵያዊያን የፓለቲካ ድርጅቶች ያጣነውን ድርጅታዊ ጥንካሬ ግንቦት 7 ለማምጣት ጥረት እያደረገ ነው። በንቅናቄው ውስጥ ቅራኔዎች ቢነሱ እንደእስከዛሬው መራኮትና መበታተን ሳይኖር በቅራኔዎች ጎልብቶ የመውጣት አቅምን እያዳበረ ያለ ድርጅት ገንብተናል ብዬ አምናለሁ።

ይህ ማለት ግን ሁሉም ነገር ተስተካክሏል ማለት አይደለም። ከድርጅት አንፃር ግንቦት 7 የሚቀሩት በርካታ ነገሮች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ጠቅሼ ንግግሬን ልጨርስ። ድርጅታዊ ብቃትን ከማሳደግ አኳያ የሚከተሉትን በቶሎ መከወን አለብን ብዬ አምናለሁ

1. ግልጽ እና አጓጊ የለውጥ ፍላጎት በአባላት ውስጥ ማሳደር እና የአጣዳፊነት ስሜት መፍጠር፣
2. በየደረጃው ጠንካራ የሥራ አስፈፃሚ መኖር እና የአባላት ጽናትን ማጎልበት፣
3. ተስማሚ ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር እና የክትትል ሥርዓት ማበጀት፣
4. የአባሎቻቸንና የሕዋሶቻችንን አቅም ገንብተን ለለውጥ ማዘጋጀት፣
5. የአጫጭር ጊዜ ድሎችን እየፈጠርን መጠናከር እና ለትላልቅ ለውጦች መዘመት፣
6. ድርጅታዊ ባህል እና የለውጥ ሂደት ተደጋጋፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
7. አካባቢን የመመዘን ችሎታችንን ማሳደግ፣ እና
8. እርስ በርሳችም ከሕዝባችንም ጋር ያለንን ሁሉን ዓቀፍ ግኑኝነት ማጠናከር።

እነዚህ ጊዜ የማይሰጣቸው ተግባራት ናቸው።

የግንቦት 7 አደረጃጀት ወያኔን ለማስወገድ ብቃት ያለው ድርጅት ከመፍጠርም አልፎ ዘለቄታ ያለው ጠቀሜታ አለው። ግንቦት 7 ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዴት መገንባት እንዳለባቸው በሞዴልነት ልንጠቀምበት የምንችለው ተቋም ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ድግሞ ለዘላቂ አብሮነታችንና እድገታችን ሁነኛ ግብዓት ነው።

ክብራትና ክቡራን

እስከዛሬ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች መለያ ባህሪይ የሆነው መሰነጣጠቅ እና ወይም መሳነፍ ሳይደርስበት ዓለምነው ቦታ ሊያደርሰን የሚችል ድርጅት ተፈጥሯል ብዬ አምናለሁ። **ይህም ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይባላል።** ይህ ንቅናቄ ምሉዕ አይደለም። ሆኖም እየታገለ የሚማር፤ እየተማረ ደግሞ የሚታገል ድርጅት ነው። እስካሁን ያልተቀላቀላችሁን ካላችሁ ዛሬውኑ ተቀላቀሉን። ተባብረን ወያኔን አስወግደን በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን እንገንባ!!

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

አፕሪል 10 ሙኒክ ላይ የቀረበ ንግግር

---

## የሊቢያ፣ ባህሬይን፣ ኢራን፣ የመንና፣ ዮርዳኖስ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢራናዊያን ይህን ህዝባዊ አመጽ ሲጀምሩ በግብፅና ቱኒዚያ ለተከናወኑ ሰልፎች ድጋፍ ለመስጠት እንደነበረ ቢገልጹም ወደ ሁዋላ ግን ሰልፈኞቹ ሞት ለአምባገነኖች የሚሉ የተቃውሞ መፈክሮችን ያሰሙ እንደነበረም ተጠቅሷል። ቀደም ብሎ የኢራን መንግስት በግብፅና በቱኒዚያ የተከናወኑ ህዝባዊ አመፆችን እንደሚደግፍ በተደጋጋሚ ቢገልጽም በሀገሩ የሚገኙ ተቃዋሚዎች በተመሳሳይ መልኩ ለግብፅና ቱኒዚያ ድጋፋቸውን ለማሳየት የጠሩትን ሰልፍ ማገዱ በርካቶችን አስገርሙአል:: በኢራን እገዳውን ጥሰው በሺዎች የሚቆጠሩ ሰልፈኞች አደባባይ ሲወጡ፤ መንግስት ወዲያውኑ የተንቀሳቃሽ ስልኮችን፣ ኢንተርኔትንና የተቃዋሚ ድረ-ገፆችን ከአገልግሎት ውጪ አድርጓቸዋል። ተንቀሳቃሽ ስልኮችና ኢንተርኔት የፕሬስ ነፃነት በሌለባት ኢራን ተቃውሞን ለመግለፅ በዋነኛ ልሳንነት ማገልገላቸው ይታወቃል። የኢራን ወታቶች በአንፃሩ መንግስት በብቸኛነት ፕሮፓጋንዳ የሚነዛባቸውን ድረ-ገፆች ማሰናከላቸውም ተዘግቧል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዘዳንት ባራክ ኦባማ የኢራን መንግስት ለውጥ ፈላጊዉን የኢራን ሰላማዊ ህዝብ ጥያቄ በአግባብ በማስተናገድ ፋንታ ተገቢ ያልሆነ ርምጃ መውሰዱን አውግዘው ዩናይትድ ስቴትስ የኢራን ህዝብን ትግል የምትደግፍ መሆናቸውን አስታውቀዋል::

በሌላም በኩል ተመሳሳይ ህዝባዊ አመጾች ሰሞኑን በሊቢያ የመንና ባህሬይን እየተካሄዱ ይገኛሉ:: በሊቢያው ተቃውሞ ሰልፍ በመንግስት ተቃዋሚዎችና በመንግስት ደጋፊዎች መካከል በተነሳ ግጭት ከአስራ አራት ሰው በላይ ተጎድቱአል:: የሊቢያ መንግስት ቴሌቪዥን ህዝባዊ አመጹን ሳይሆን የሊቢያ መንግስት ደጋፊ የሆኑ ጥቂት ሰልፈኞችን እንቅስቃሴ ብቻ እየዘገበ እንደሚገኝም ታውቁአል:: በተመሳሳይ መልኩ በየመን በተቃዋሚ ሰልፈኞችና በመንግስት ደጋፊዎች መካከል ከፍተኛ ግጭት ተነስቶ በርካቶች መቁሰላቸው ተዘግቡአል:: በባህሬይንም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰልፈኞች የሃገራቸው መንግስት ቁንጮ ስልጣን እንዲለቁና ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራቸው እንዲሰፍን ድምጻቸውን እያሰሙ ሲሆን፣ ተቃዋሚዎችን ለመበተን ፖሊስ በወሰደው ርምጃ ሁለት ሰዎች መሞታቸው ታውቁአል::

ይህን በሰሜን አፍሪቃ እንደሰድድ እሳት እየተቀጣጠለ ያለ ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያችንም ሊፈነዳ እንደሚችል በርካታ ፍንጮች እየታዩ ነው።

## መለስ እና ግብረ አበሮቹ አደረግን ያሉት ... (ከገጽ 1 የዞረ)

በከፍተኛ ሁኔታ እጥረት እየታየባቸው ካሉት ምርቶች ስኳርና የምግብ ዘይት በቀዳሚነት እንደሚጠቀሱ የሚናገሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መለስ ዜናዊና ሚስቱ እንዳሻቸው የሚያሾሩዋቸው የህወሃት ንግድ ድርጅቶች የሚቀናቀናቸውን የንግድ ድርጅቶች ከውድድር መድረክ ካባረሩ በሁዋላ ሆን ብለው ሸቀጦችን በመደበቅ ከፍተኛ የሆነ የ ዕቃ እጥረት እንዲፈጠር አድርገዋል በማለት ትንሽ ቆየት ብለው ይህንኑ ዋጋ ጨምረውበት ግዙ ሊሉን እንደሚችሉ ይጠበቃል ብለዋል ። ቀደም ሲል ወያኔ ባሰማራቸው ካድሬዎችና ሰላዮች ብሶታቸውን መናገር ይሸማቀቁ የነበሩት ነዋሪዎች ከአሁን ቦኋላ ከዚህ የሚብስ ምን ሊመጣብን ነው ከሚል ተስፋ መቁረጥ ኑሮው ከአቅማቸው ብላይ እንደሆነና መፍትሄው እንደቲንዚያና ግብጽ ህዝብ ሆ ብሎ በመነሳት የወያኔን አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ከመገላገል የተሻለ አማራጭ እንደማይገኝ በድፍረት እየተናገሩ ነው።

## ማስታወቂያ

### ለአራተኛ ጊዜ ተቋዋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭት በ24 ሰአት ውስጥ አገልግሎት መስጠቱን ቀጠለ

የካቲት 2፣ 2003 ዓም በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 5:45 ላይ ወደ ኢትዮጵያና አካባቢ ሀገራት የሚያስተላልፈው የቀጥታ ፕሮግራም ስርጭት ለአራተኛ ጊዜ እንደገና መታወኩን አስታወቆ የነበረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ያጋጠመውን ፈታኝ ችግር ተቋዋቁሞ ስርጪቱን እንደገና የጀመረ መሆኑን አስታወቀ።

ኢሳት ቀደም ብሎ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት በተቋረጠበት ወቅት ከሳተላይት ኩባንያው ጋር ተነጋግሮ የሚያገኘውን ውጤት በአስቸኳይ ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ገልጾ የነበረ ሲሆን የኢሳት ፕሮግራም የተቋረጠበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ፕሮግራሞቹን በሌላ ሳተላይት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ ለማስተላለፍ ተግቶ እንደሚሠራ ገልጾ ነበር።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የታይ ኮም ኩባንያ ሰራተኛ የኢሳትን ስርጪት መቋረጥ አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጡን አቅርበን ለነበረው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የወያኔ ባለስልጣናት ከሁለት ወር በላይ የኢሳት ስርጭት እንዲቋረጥ ካምፓኒው ላይ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማቲክ ግፊት ሲያደርጉ እንደነበር ገልጸው በስተመጨረሻው ምን ዓይነት የጥቅም ድርድር አድርገው እንደተሳካላቸው ለማወቅ አልቻልንም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን በትናንትናው እለት ባወጣው መግለጫው ታይኮም የሳታላይት ካምፓኒ ስርጪቱን ከአየር ባወረደ ሃያ አራት ሰአት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ኢንተል ሳት በተባለ ሌላ ሳታላይት ካምፓኒ አማካኝነት ወደ አየር መመለሱን ገልጾአል። አዲሱ የሳተላይት ጣቢያ ምንም ተጨማሪ ወጪ ሳያስፈልግ ትንሽ ብቻ የሳተላይት መቀበያ ሳህኑን በማዞር ማግኘት እንደሚቻል እና በዚህ በአዲሱ ኢንቴል ቻናል አልጀዚራን የመሳሰሉ ትላልቅ የተሌቪዝን ጣቢያዎችን ማግኘት እንደሚቻል ለማወቅ ተችሎአል። አዲሱን የኢሳት ፍሪኩዌንሲ ለማወቅ ለምትሹ አድማጮቻችን፤

Intelsat 10 at 68.5 East
C-band
Transponder 14
Downlink: 3808 V
Symbol rate: 10340
FEC: ¾

መሆኑን እንገልጻለን::

በቱኒዚያ ተቀጣጥሎ ግብጽንና ሌሎች የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን እያስራደ ያለው የህዝብ አመጽ እንቅልፍ የነሳው የወያኔው ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች ይህን የህዝብ አመጽ እንዳይተላለፉ ያደረገ ሲሆን ባንጻሩ በነዚህን ሃገራት የተነሳውን የህዝቦች አመጽ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በስፋት እየዘገበው በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ስጋት ውስጥ እንደከተተው ብዙዎች ይናገራሉ::

የህዝባችንን ነጻና ገለልተኛ መረጃ የማግኘት መብት አፍኖ ዕድሜ ልኩን ለመግዛት ያሰበው ወያኔ ከዚህም በፊት በአረብ ሳት አማካኝነት ይተላለፈ የነበረውን ስርጭት ከካምፓኒው ጋር በመደራደርና ከፍተኛ ገንዘብ በመክፈል እንዳሰናከለው ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ ወይም በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org